# የመመሥረቻ ጽሑፍ

## አንቀጽ አንድ

### ማቋቋም

ለአነስተኛ ገበሬዎችና በአነስተኛ የማምረት ሥራ ላይ ለተሠማሩ ሰዎች የኢኮኖሚ ዕድገት በቀላሉ የሚገኝ የገንዘብ ምንጭ ወሳኝ መሆኑን በመረዳት፣

በአንስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች ከዚህ የገንዘብ ምንጭ በቀላሉ ገንዘብ ቢበደሩ የራሳቸውን ገቢ በመፍጠር፣ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደርና በራስ መተማመንን የሚያጐለብቱ መሆኑን በመገንዘብ፣

እንደዚሁም ለአነስተኛ ብድር አቅራቢ የገንዘብ ድርጅቶች ፈቃድ ለመስጠትና ሥራቸውን ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 40/1989 በመበረታት፣

እኛ ስማችን ዜግነታችንንና አድራሻችን በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ ሁለት ሥር የተጠቀሰው ይኸንን የአክሲዮን ማህበር አቋቁመናል:: የአክሲዮን ማህበሩም የሚተዳደረው በዚሁ አዋጅና በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ መሠረት የሆናል::

## አንቀጽ ሁለት

### የመሥራች አባሎች ዜግነት፣

### አድራሻና የአክሲዮን ድርሻ

| ስም | ዜግነት | አድራሻ | የአክስዮን ብዛት | ቃል የተገባ ብር | የተከፈለ ብር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. ኦሮሞ ራስ አገዝ ማኀበር (ኦስራ) | ኢትዮጵያዊ | አዲስ አበባ | 400 | 40,000 | 40,000 |
| 2. በቀለ ወልዴ ጋሪዮ | " | " | 270 | 27,000 | 27,000 |
| 3. ብርሃኑ ዲሣሣ ዱቲ | " | " | 268 | 26,800 | 26,800 |
| 4. ብርሃኑ ደበሌ አባወያ | " | " | 268 | 26,800 | 26,800 |
| 5. ታዲ ሊበን ኑራ | " | " | 268 | 26,800 | 26,800 |
| 6. ተረፈ በየነ ረቅቱ | " | " | 268 | 26,800 | 26,800 |
| 7. ተሰማ ያኢ ዱላ | " | " | 268 | 26,800 | 26,800 |
| ጠቅላላ | | | 2010 | 201,000 | 201000 |

## አንቀጽ ሦስት
## የአክሲዮን ማህበሁሩ ስም

የአክስዮን ማህበሩ ወሳሳ የአነስተኛ ብድር አቅራቢ ገንዘብ ድርጅት ተብሎ ይጠራል።

## አንቀጽ አራት

የድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 18 ቀበሌ 41 የቤት ቁጥር 377 ነው። ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በዞንና በወረዳዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎችን ሊከፍት ይችላል።

## አንቀጽ አምስት
## የድርጅቱ ዓላማዎች

የድርጅቱ ዓላማዎች የሚከተሉትን ይጨምራል።

5.1 በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ለገበሬዎች፣ ለሴቶች፣ ለወጣቶችና በአነስተኛ ሥራ ላይ ለተሠማሩ የሕብረት ሥራ ማህበሮች ብድር መስጠት፣

5.2 በቁጠባና በተቀማጭነት ገንዘብ መቀበል፣

5.3 በኢትዮጵያ ውስጥ በሐዋላ ገንዘብ የማስተላለፍ ሥራ መሥራት፣

5.4 ገቢ ለማግኘት እንደ ትሬዠሪ ቢልስ ያሉትን መንግሥት የሚያወጣቸውን የገንዘብ ሰነዶች መግዛት፣

5.5 ለሥራው የሚያስፈልጉ ቢሮዎችንና መኖሪያ ቤቶችን እንደዚሁም ማንኛውንም የሚንቀሳቀሱትንና የማይንቀሳቀሱትን ንብረቶች ለመግዛት ለመጠገን፣ ለመሸጥና ለሌላ ለማስተላለፍ፣

5.6 ለደምበኞች የምክር አገልግሎት ለማስጠት፣

5.7 አነስተኛ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች በገጠርና በከተማ እንዲስፋፉ ማበረታታት፣

5.8 የማኔጅመንት፣ የገበያ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ምክር ለተበዳሪዎች መስጠትና እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ መርዳት፣

5.9 አገር አቀፍ የቁጠባ በህል እንዲዳብር መቀስቀስ፣

5.10 ከዓላማው ጋር በተገናኙ በማንኛውም ተግባርና በተለይም ከአነስተኛ ብድር ድርጅት ጋር ግንኙነት ባላቸው ሥራዎች ላይ መሠማራት፣

## አንቀጽ ስድስት
## የድርጅቱ ካፒታል

6.1 የድርጅቱ ካፒታል ብር 201000 /ሁለት መቶ አንድ ሺ ነው/:: የድርጅቱ ካፒታል በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል::

6.2 የድርጅቱ ካፒታል አክስዮኖችን በመሸጥ ሊያድግ ይችላል::

## አንቀጽ ሰባት

7.1 ድርጅቱ አንድ ደረጃ ያላቸው የያንዳንዱ ዋጋ ብር 100 የሆነ 2010 አክሲዮኖች አሉት::

7.2 አክሲዮኖች የሚሰጡትና የመዘገቡት በባለአክሲዮኖች ስም ነው:: ላመጪው የሚከፈሉ አክሲዮኖች አይኖሩም ወይም የተከለከሉ ናቸው::

7.3 አክሲዮች አይከፋፈሉም በአንድ የተፈጥሮ ሰው የሚያዝ አነስተኛ የአክሲዮን ቁጥር አንድ ነው::

## አንቀጽ ስምንት
## የባለአክዮኖች ኃላፊነት

የባለአክሲዮኖች ኃላፊነት በድርጅቱ ውስጥ ባላቸው የአክሲዮኖች ብዛት ይወሰናል::

## አንቀጽ ዘጠኝ
## የትርፍ ክፍያ

9.1 የድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ከገቢው ላይ ማናቸውም ውጪ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ገንዘብ ነው:: ይኸም በዓመቱ የሂሳብ መዝገበ ውስጥ እንደሚታየወ ይሆናል::

9.2 ከድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ውስጥ የሚከተሉት በተለይ ይቀመጣሉ

5%

ሀ/ ከትርፉ ሃያ አምስት በመቶ /25%/ በያመቱ ወደ ተጠባባቂ ሂሳብ ይዛወራል:: ይህም የሚሆነው ብተጠባባቂ ሂሳብ ውስጥ የተቀመጠው ገንዘብ የድርጅቱ ካፒታል ሃምሣ በመቶ /50%/ እስኪሆን ድርስ ነው::

ለ/ ከተጣራ ትርፍ አምስት በመቶ /5%/ ለቦርድ ዲሬክተሮች አበል ክፍያ እንዲውል ለብቻው ይቀመጣል::

9.3 ከተጣራው ትርፍ ቀሪ ገንዘበ በጠቅላላው ስበሰባ ውሳኔ መሠረት በማህበሩ ውስጥ ባላቸው የአክሲዮን ድርሻ መጠን ለባለአክሲዮኖች ይከፋፈላል::

## አንቀጽ አሥር
## የድርጅቱ የአስተዳደር አካላት

10.1 ድርጅቱ የሚከተሉት የአስተዳደር አካላት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የባለአክስዮኖች ጉባዔ
ለ/ የዲሬክተሮች ቦርድ
ሐ/ ዋና ሥራ አስኪያጅ
መ/ ኦዲተር

10.2 የጠቅላላ ጉባዔው፣ የዋናው ሥራ አስኪያጅና የኦዲተሩ ሥልጣንና ኃላፊነት በሕግና በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ በተሰጠው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ
## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

11.1 የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የድርጅቱ የበላይ አካል ነው፡፡

11.2 ጠቅላላ ጉባዔው አግባብ ባላቸው በማናቸውም ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይ ሥልጣን አለው፡፡

11.3 ፖሊሲዎችን ይቀይሳል

11.4 የዲሬክተሮች ቦርድ አባሎችን ይሾማል፣ ከሥራም ያሰናብታል፡፡

11.5 ይኸንን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል ይችላል፡፡

11.6 የዓመት ዕቅዶችን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

## የዲሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ኃላፊነት

12.1 የዲሬክተሮች ቦርድ ከባለአክሲዮኖች መካከል የተመረጡ አምስት /5/ አባሎች ይኖሩታል

12.2 የመጀመሪያ የዲሬክተሮች ቦርድ አባሎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1    አስራ /በአቶ በቀለ ወልዴ በመወከል/
2 አቶ ብርሃኑ ዲሣሣ ዶቲ
3 " ተረፈ በየነ ረቅቱ
4 " ታዲ ሊበን ኑራ
5 " ተሰማ ያኢ ዱላ

12.3 የቦርድ ዲሬክተሮች የሥራ ዘመን ሦስት/3/ዓመት ይሆናል፡፡ የሥራ ዘመኑን የጨረሰ የዲሬክተሮች ቦርድ አባል በድጋሚ ሊመረጥ ይችላል፡፡

12.4 የዲሬክተሮች ቦርድ ከጠቅላላ ጉባዔው ቀጥሎ የድርጅቱን ሥራ ለማከናወን ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡

12.5 በዚህ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር 12.4 ሥር የተሰጠው ጠቅላላ ሥልጣን እንደ ተጠበቀ ሆኖ የዲሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣን ይኖሩታል።

ሀ/ ዋናውን ሥራ አስኪያጅ መሾም ፣ ከሥራው ማሰናበት፣ ደሞዙንና አበሉን መወሰን፣

ለ/ የድርጅቱን በጀት ማፅደቅ፣

ሐ/ የድርጅቱን ንብረት መሸጥ፣ በዋስትና ማስያዝ፣

መ/ በብድር አሰጣጥ ላይ መመሪያ መስጠት፣

ሠ/ የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባ መጥራት፣

ረ/ በጠቅላላ ጉባኤ ስወከል ፖሊሲ ነክ በሆነ የድርጅቱ ጉዳዮች ሁሉ ላይ ውሳኔ መስጠት

12.6 የቦርዱ ልቀመንበር የጠቅላላ ጉበዔውን ስበሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል።
12.7 የቦርዱ አባሎች በሚጉድሉበት ጊዜ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ይተካሉ ።

## አንቀጽ አስራ ሦስት
## የድርጅቱ ሥራ አመራር

13.1 ድርጅቱ የሚመራው በዲሬክተሮች ቦርድ በተመረጠ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው።

13.2 ዋና ሥራ አስኪያጅ ለድርጅቱ የዕለት ተዕለት ሥራ ክንውን ኃላፊ ነው።

13.3 ዋናው ሥራ አስኪያጅ ሌሎች ተግባሮችን ከዲሬክተሮች ቦርድ በውክልና በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ያከናውናል።

13.4 ዋና ሥራ አስክያጁ ለድርጅቱ የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች ይቀጥራል።

## አንቀጽ አሥራ አራት
## ኦዲተር

14.1 ድረጅቱ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ኦዲተር ይኖረዋል።
14.2 የኦዲተሩ ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ ከቁጥር 373-380 ሥር በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል።
14.3 የኦዲተሩ የአገልግሎት ክፊያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል።

## አንቀጽ አሥራ አምስት

## የበጀት ዓመትና ሪፖርት

15.1 የድርጅቱ የበጀት ዓመት እ.አ.አ. በያመቱ ከጥር 1 ቀን እስከ ታህሳስ 31 ቀን ይሆናል ሆኖም የመጀሪያው ዓመት በጀት የድርጅቱ ምዝገባ ከተፈፀመበት ቀን ይጀመራል።
15.2 የድርጅቱ ዓመታዊ ሪፖርትና የኦድተር ሪፖርት የበጀት ዓመቱ ካለቀ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይቀርባል።

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

## የሕጎች ተፈጻሚነት

በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍና በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በግልጽ ባልተቀመጡ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ አግባብ ያላቸው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ ሌሎች ሕጉችና ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ አሥራ ሰባት

## ድርጅቱ የተቋቋመበት ጊዜ

በንግድ ሕግ ቁጥር 495 ሥር ከተጠቀሱት ምክንያቶች መካከል በአንዱ ወይም በሌላ ምክንያት ካለፈረሰ በስተቀር ድርጅቱ የዕድሜ ገደብ የለውም።

እኛ ስማችንንና ፊርማችንን ከዚህ በታች ያሠፈርነው የወሳሳ አነስተኛ ብድር ድርጅት መሥራች አባሎች ይኸንን የመመሥረቻ ጽሑፍ ዛሬ ቀን 1991 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አጽድቀናል።

| ተ.ቁ | ስም | ፊርማ |
| --- | --- | --- |
| 1. | አስራ/በቀለ ወልዴ ጋሪዮ | |
| 2. | በቀለ ወልዴ ጋሪዮ | |
| 3. | ብርሃኑ ጂማማ ዶቲ | |
| 4. | ብርሃኑ ድበሌ አባወይ | |
| 5. | ታዲ ሊበን ኑራ | |
| 6. | ተረፈ በየነ ረቅቁ | |
| 7. | ተሰማ ያኢ ዱላ | |

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፣
በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር
የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ

ቁጥር 167/41/92

በጽሕፈት ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል

ቀን 16/12 ቀን ፲፱ 92 ዓ.ም

ይርጋ ታደሰ
የውልና ማስረጃ ምዝገባ
ጽ/ቤት ኃላፊ